# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

በኤፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀፅ 97/2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራትን ለማስጠበቅና አዋጁን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገው የሚከተሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ነው።

1) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አግባብነት ካላቸው የመንግስት መመሪያዎችና ደንቦች እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 ዓ.ም አኳያ ለሚያደርጉት የደረጃ ስያሜና ለውጥ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ለመውሰድ የሚያስችላቸውን ሥርዓት ለመዘርጋት እና
2) የደረጃ ስያሜ ጥያቄ የሚያቀርቡ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን መመዘኛ በትክክል አውቀው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ጥያቄያቸውን ማቅረብ የሚችሉበትን ሥርዓት ለመዘርጋት ነው።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

በአዋጁ አንቀፅ 11፣12፣13 እና 14 መሠረት የዩኒቨርሲቲ፣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ የኮሌጅ እና የኢንስቲትዩት የደረጃ ስያሜ ጥያቄ ለሚያቀርቡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመመሪያው በተመለከቱት መስፈርት የሚመጥናቸውን የደረጃ ስያሜ መስጠት ነው።

## 4. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የደረጃ ስያሜ አሰጣጥ መመሪያ 577/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 5. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

5.1 "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው።

5.2 "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው።

5.3 "ከፍተኛ ትምህርት " ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተውን ትርጉም ይይዛል።

5.4 -"ተቋም" ማለት  የመንግስት ወይም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው።

5.5 "ኤጀንሲ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው።

5.6 "ዩኒቨርሲቲ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ተቋም ሊያገኘው የሚችለው የደረጃ ስያሜ ነው።

5.7 "ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ተቋም ሊያገኘው የሚችለው የደረጃ ስያሜ ነው።

5.8 "ኮሌጅ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 13 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ተቋም ሊያገኘው የሚችለው የደረጃ ስያሜ ነው።

5.9 "ኢንስቲትዩት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ተቋም ሊያገኘው የሚችለው የደረጃ ስያሜ ነው።

5.10 "ፋኩልቲ" ማለት በአንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ከአንድ በላይ  የስልጠና መስኮች ወይም ዲፓርትመንቶች ያለው የተቋሙ አካል ነው።

5.11 "ትምህርት ቤት" ማለት በአንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ በአንድ የስልጠና መስክ ወይም ዲፓርትመንት ልዩ ስልጠና (Specialization) የሚያካሂድ የተቋም አካል ወይም በአንድ የስልጠና መስክ ብቻ የከፍተኛ ትምህርት ሥልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው።

## 6. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 7. አስፈፃሚው አካል

በአዋጁ አንቀፅ 11፣12፣13 እና 14 መሠረት የተቋማት የደረጃ ስያሜ በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሲሆን በአንቀጽ 89 መሠረት የተቋማት የደረጃ ስያሜን በተመለከተ ኤጀንሲው የሚቀርብለትን የደረጃ ስያሜ ጥያቄ በመገምገም ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

# ክፍል ሁለት

# የተቋማት የደረጃ ስያሜ አሰጣጥ

## 8. መርሆዎች

8.1 ማንኛውም ተቋም በአዋጁ አንቀጽ 11፣ 12፣ 13 እና 14 መሰረት የደረጃ ስያሜ ካልተሰጠው በስተቀር የደረጃ ስያሜን ያለ ትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ መስጠት አይችልም።

8.2 በሚኒስቴሩ ባልጸደቀ ስያሜ የሚሰጥ የትምህርት ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

8.3 ማንኛውም ተቋም ኤጀንሲው ለደረጃ ስያሜ አሰጣጥ የሚጠይቃቸውን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል።

8.4 ተቋሙ ከከፍተኛ ትምህርት ውጪ (እንደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የመሳሰሉት) ስልጠናዎችን የሚሰጥ ከሆነ በውስጡ ከፍተኛ ትምህርት ለመስጠት በሚያስችል ራሱን በቻለ አደረጃጀት የተዋቀረ መሆን አለበት።

## 9. የዩኒቨርሲቲ ደረጃን ስለማግኘት

ዩኒቨርሲቲ ሆኖ የሚቋቋም ወይም ወደ ዩኒቨርሲቲነት የሚያድግ ማንኛውም ተቋም "ዩኒቨርሲቲ" የሚለውን የደረጃ ስያሜ በሚኒስቴሩ የሚሰጠው ሆኖ ይህን የደረጃ ስያሜ ለማግኘት የሚያመለክት ተቋም የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል።

### 9.1 በመደበኛ መርሀ ግብር ተማሪዎችን የማስተማር አቅምን በተመለከተ

በመደበኛው ፕሮግራም በዲግሪና ከዚያ በላይ በሆኑ መርሀግብሮች ቢያንስ ሁለት ሺህ ተማሪዎችን የመቀበልና የማስተናገድ አቅም ያለው መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም እንደመረጃ ምንጭነት የሚከተሉትን ማቅረብ ይጠበቅበታል።

1) ተቋሙ 2 ሺ. ተማሪዎች የመቀበል አቅም ያለው መሆኑን ወይም ተቀብሎ በማስተማር ላይ ያለ መሆኑን የሚያመለክቱ የቁሳቁስ፣ የሰው ሃይልና የፋይናንስ አቅም መረጃዎችን ሊያቀርብ ይገባል።

2) በየስልጠና መስኩ የተመዘገቡና በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ስም ዝርዝር በተቋሙ ሬጅስትራር መቅረብ አለበት።

## 9.2 በዲግሪ መርሀ ግብር የማስመረቅ ሁኔታን በተመለከተ

በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት ወይም በኮሌጅነት ወይም በኢንስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ተቋም ከሆነ በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለአራት ተከታታይ ዓመታት ተማሪዎችን ማስመረቅ ያለበት ሲሆን ይህን የሚያመለክቱ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል።

1) በተቋሙ ሬጅስትራር የተዘጋጀ የ4ቱን ዓመታት ተመራቂ ተማሪዎች ስም ዝርዝር በተመዘገቡበት የስልጠና መስክና የትምህርት ዘመን ከነማጠቃለያው (summary)፣
2) የ4ቱም ዓመታት ምረቃው የጸደቀበት የተቋሙ ሰኔት ወይም የአካዳሚክ ኮሚሽን ቃለ ጉባኤ እና
3) የምረቃ መጽሔት (graduation bulletin) ማቅረብ አለበት።

## 9.3 የፋኩልቲዎች/የኮሌጆች/የኢንስቲትዩቶችን ብዛትና ስብጥር በተመለከተ

ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች (ፋኩልቲ፣ኮሌጅ፣ትምህርት ቤት፣ኢንስቲትዩት) በተለያዩ ሙያዎች በዲግሪ እና ከዚያ በላይ ባሉ መርሐግብሮች ወይም ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ አራት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

1) የፋኩልቲ፣ኮሌጅ፣የኢንስቲትዩት ወይም የትምህርት ቤቶቹ አወቃቀርና በስራቸው ያሉ የትምህርት ክፍሎችና ተጠሪነታቸው፣
2) ተቋሙ ያለው የፋኩልቲ እና ሌሎች የትምህርት ክፍሎች ዝርዝር፣
3) በየፋኩልቲው፣ ኮሌጅ ወይም ኢንስቲትዩት በመጨረሻው 1 ሴሚስተር ውስጥ የተያዙት ቃለ ጉባኤዎች እና
4) በየትምህርት ክፍሉ አሁን በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ብዛት።

## 9.4 የምርምር ስራን በተመለከተ

አግባብነት ባላቸው የተለያዩ መስኮች የሕብረተሰቡን ችግር መሠረት ያደረጉ ምርምሮችን ማድረግ፣ የታተሙ የምርምር ውጤቶች መኖርና የምርምር ውጤቱንም ለተጠቃሚው የሚያስተላልፍበት መንገድ ያመቻቸ መሆን ይጠበቅበታል። ለዚህም እንደ መረጃነት የሚያገለግሉ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅበታል።

1) የምርምር ስትራቴጂ ዶክመንት፣
2) የታተሙ ጆርናሎችና ፕሮሲዲንግስ፣
3) መምህራኑ በጥናትና ምርምር ዙሪያ ያላቸው ተሳትፎና ውጤት የሚያመላክት ሰነድ፣
4) የምርምር ውጤቶችን የሚያሰራጭበት ስርዓትና አተገባበር የሚያመላክት ሰነድ፣
5) የተደረጉ ዓመታዊ አካዳሚክ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች ዓይነት፣ ብዛትና አፈፃፀም የሚያመላክት ሰነድ እና
6) በምርምር የተገኙና ለኢንዱስትሪዎች የተላለፉ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር።

## 9.5 ለስራው አስፈላጊ የሆኑና ለደረጃው የሚመጥኑ ግብአቶችን በተመለከተ

1) **የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና አስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው፡፡**

   ሀ) በዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የመምህራን ብዛትና ስብጥር በትምህርት ደረጃና በአካዳሚክ ማዕረግ፣

   ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት እና

   ሐ) የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስታትስቲክስ።

2) **የተቋሙን ኢንፍራስትራክቸርና ሌሎች ግብአቶችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

   ሀ) ለደረጃው የተቀመጠውን የተማሪዎች ቁጥር ማስተናገድ የሚችሉና በቴክኖሎጂ በተደገፉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት፣

   ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑና የተደራጁ ወርክሾፖች ብዛት፣

ሐ) እንደየሙያው አስፈላጊነት በተገቢው ዕቃዎች፣ ማንዋሎችና ኬሚካሎች የተደራጁ እና ከማንኛውም አደጋ የተጠበቁ ቤተሙከራዎች ብዛት፣

መ) በኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍትና ጆርናሎች የተደራጀ ቤተመጽሐፍት፣

ሠ) የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦች (legislation) ፣ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣይ ዓመት ስትራቴጂና ዕቅድ።

### 9.6 የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላትን በተመለከተ

1) ቀደም ብሎ የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መመዘኛዎችን አሟልቶ በኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

## 10. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ደረጃን ስለማግኘት

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሆኖ የሚቋቋም ወይም ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት የሚያድግ ማንኛውም ተቋም "ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ" የሚለውን የደረጃ ስያሜ በሚኒስቴሩ የሚሰጠው ሆኖ ይህን የደረጃ ስያሜ ለማግኘት የሚያመለክት ተቋም የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል።

### 10.1 በመደበኛ መርሀ ግብር ተማሪዎችን የማስተማር አቅምን በተመለከተ

በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ሁለት ሺህ ተማሪዎችን በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የማስተማር አቅም ያለው ሊሆን የሚገባ ሲሆን ለዚህም እንደመረጃ ምንጭነት የሚከተሉትን ማቅረብ ይጠበቅበታል።

1) ተቋሙ 2 ሺ ተማሪዎች የመቀበል አቅም ያለው መሆኑን ወይም ተቀብሎ በማስተማር ላይ ያለ መሆኑን የሚያመለክቱ የቁሳቁስ፣ የሰው ሃይልና የፋይናንስ አቅም መረጃዎችን ሊያቀርብ ይገባል።
2) በየስልጠና መስኩ የተመዘገቡና በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ስም ዝርዝር በተቋሙ ሬጅስትራር መቅረብ አለበት።

## 10.2 በዲግሪ መርሀ ግብር የማስመረቅ ሁኔታን በተመለከተ

በኮሌጅነት ወይም በኢንስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ተቋም ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም እንደመረጃ ምንጭነት የሚከተሉትን ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

1) በተቋሙ ሬጅስትራር የተዘጋጀ የሶስቱን ዓመታት ተመራቂ ተማሪዎችን ስም ዝርዝር በየመርሐ ግብሩ በተመዘገቡበት የስልጠና መስክና የትምህርት ዘመን ከነማጠቃለያው (summary)፣
2) የሶስቱን ዓመታት ምረቃው የጸደቀበት የሴኔት ወይም የአካዳሚክ ካውንስል ቃለ ጉባኤ እና
3) የምረቃ መጽሔት (graduation bulletin)፡፡

## 10.3 የፋኩልቲዎች/የኮሌጆች/የኢንስቲትዩቶችን ብዛት በተመለከተ

ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች(ፋኩልቲ፣ኮሌጅ፣ትምህርት ቤት፣ኢንስቲትዩት) በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ በተለያዩ ሙያዎች ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም እንደመረጃ ምንጭነት የሚከተሉትን ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

1) የፋኩልቲ፣ የኮሌጅ፣ የኢንስቲትዩት ወይም የትምህርት ቤቶቹ አወቃቀርና በስራቸው ያሉ የትምህርት ክፍሎችና ተጠሪነታቸው የሚያመለክት ሰነድ፣
2) ተቋሙ ያለው የፋኩልቲ እና ሌሎች የትምህርት ክፍሎች ዝርዝር፣
3) በየፋኩልቲው፣ኮሌጅ ወይም ኢንስቲትዩት በመጨረሻው 1 ሴሚስተር ውስጥ የተያዙት ቃለ ጉባኤዎች እና
4) በየትምህርት ክፍሉ አሁን በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ብዛት፡፡

## 10.4 የምርምር ስራን በተመለከተ

አግባብነት ባላቸው የተለያዩ መስኮች የሕብረተሰቡን ችግር መሠረት ያደረጉ ምርምሮች ማድረግ፣ በተቋሙ የታተሙ የምርምር ውጤቶች መኖርና የምርምር ውጤቱን ለተጠቃሚው የሚያስተላልፍበትን መንገድ ያመቻቸ ሊሆን ይገባል፡፡ ለዚህም እንደ መረጃነት የሚያገለግሉ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊያቀርብ ይገባል፡፡

1) የምርምር ስትራተጂ ዶክመንት፣
2) የታተሙ ጆርናሎች፣ ፕሮሲዲንግስ፣
3) መምህራኑ በጥናትና ምርምር ዙሪያ ያላቸው ተሳትፎና ውጤት የሚያመላክት ሰነድ፣
4) የምርምር ውጤቶችን የሚያሰራጭበት ስርዓትና አተገባበር የሚያመላክት ሰነድ፣
5) የተደረጉ ዓመታዊ አካዳሚክ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች ዓይነት፣ ብዛትና አፈፃፀም የሚያመላክት ሰነድ እና
6) በምርምር የተገኙና ለኢንዱስትሪዎች የተላለፉ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር።

## 10.5 ለስራው አስፈላጊ የሆኑና ለደረጃው የሚመጥኑ ግብአቶችን በተመለከተ

1) **የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

ሀ) በዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የመምህራን ብዛትና ስብጥር በትምህርት ደረጃና በአካዳሚክ ማዕረግ፣

ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት እና

ሐ) የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስታትስቲክስ።

2) **የተቋሙን ኢንፍራስትራክቸርና ሌሎች ግብአቶችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

ሀ) የተቋሙን ተማሪ ማስተናገድ የሚችሉና በቴክኖሎጂ በተደገፉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት፣

ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑና የተደራጁ ወርክሾፖች ብዛት፣

ሐ) እንደየሙያው አስፈላጊነት በተገቢው ዕቃዎች፣ ማንዋሎችና ኬሚካሎች የተደራጁ እና ከማንኛውም አደጋ የተጠበቁ ቤተሙከራዎች ብዛት፣

መ) በኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍትና ጆርናሎች የተደራጀ ቤተመጽሐፍት እና

ሠ) የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦች(legislation)፣ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣይ ዓመት ስትራቴጂና ዕቅድ።

## 10.6 የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላትን በተመለከተ

1) ቀደም ብሎ የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መመዘኛዎችን አሟልቶ በኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

# 11. የኮሌጅ ደረጃን ስለማግኘት

## 11.1 በመደበኛ መርሀ ግብር ተማሪዎችን የማስተማር አቅምን በተመለከተ

ኮሌጅ ሆኖ የሚቋቋም ወይም ወደ ኮሌጅነት የሚያድግ ማንኛውም ተቋም በትምህርት ሚኒስቴር "ኮሌጅ" የሚለውን የደረጃ ስያሜ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል።

1) ቢያንስ በአንድ ፋኩልቲ የከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ መሆን አለበት።
2) በዲግሪ መርሐ ግብር ደረጃ ትምህርትና ስልጠና የመስጠት አቅም ያለው መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል።

   ሀ) የሚያስተምርበትን የስልጠና መስክ ዓይነትና ያደረገውን ቅድመ ዝግጅት በዝርዝር ማሳወቅ አለበት።

   ለ) ተቋሙ በተጠቀሰው የዲግሪ መርሐ ግብር ትምህርት የመስጠት አቅሙን የሚያመለክቱ መረጃዎች ወይም የፋሲሊቲ ዝርዝር ሊያቀርብ ይገባል።

## 11.2 ለስራው አስፈላጊ የሆኑና ለደረጃው የሚመጥኑ ግብአቶችን በተመለከተ

1) **የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

   ሀ) በዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የመምህራን ብዛትና ስብጥር በትምህርት ደረጃና በአካዳሚክ ማዕረግ፣

   ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት እና

   ሐ) የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስታትስቲክስ።

2) **የተቋሙን ኢንፍራስትራክቸርና ሌሎች ግብአቶችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

   ሀ) የተቋሙን ተማሪ ማስተናገድ የሚችሉና በቴክኖሎጂ በተደገፉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት፣

   ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑና የተደራጁ ወርክሾፖች ብዛት፣

ሐ) እንደየሙያው አስፈላጊነት በተገቢው ዕቃዎች፣ ማንዋሎችና ኬሚካሎች የተደራጁ እና ከማንኛውም አደጋ የተጠበቁ ቤተሙከራዎች ብዛት፣

መ) በኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍትና ጆርናሎች የተደራጀ ቤተመጽሐፍት እና

ሠ) የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦች(legislation)፣ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣይ ዓመት ስትራቴጂና ዕቅድ።

### 11.3 የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላትን በተመለከተ

1) ቀደም ብሎ የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መመዘኛዎችን አሟልቶ በኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

## 12. የኢንስቲትዩትነት ደረጃን ስለማግኘት

አንድ ተቋም ከትምህርት ሚኒስቴር "ኢንስቲትዩት" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል።

### 12.1 በመደበኛ መርሀ ግብር ተማሪዎችን የማስተማር አቅምን በተመለከተ

1) ቢያንስ በአንድ የትምህርት ወይም የስልጠና መስክ ትምህርትና ስልጠና መስጠት መቻል አለበት።

2) በዲግሪ ደረጃ ትምህርት የመስጠት አቅም ያለው መሆን ያለበት ሲሆን ለዚህም እንደመረጃ ምንጭነት የሚከተሉትን ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሀ) የሚያስተምርበትን የስልጠና መስክ ዓይነትና ያደረገውን ቅድመ ዝግጅት የሚያመለክት ማስረጃ በዝርዝር ማሳወቅ አለበት።

### 12.2) ለስራው አስፈላጊ የሆኑና ለደረጃው የሚመጥኑ ግብአቶችን በተመለከተ

1) **የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው።**

ሀ) በዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የመምህራን ብዛትና ስብጥር በትምህርት ደረጃና በአካዳሚክ ማዕረግ እና

ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት።

2) **የተቋሙን ኢንፍራስትራክቸርና ሌሎች ግብአቶችን በተመለከተ የሚከተሉት መቅረብ አለባቸው፡፡**

ሀ) የተቋሙን ተማሪ ማስተናገድ የሚችሉና በቴክኖሎጂ በተደገፉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት፣

ለ) እንደየስልጠና መስኩ አስፈላጊ የሆኑና የተደራጁ ወርክሾፖች ብዛት፣

ሐ) እንደየሙያው አስፈላጊነት በተገቢው ዕቃዎች፣ ማንዋሎችና ኬሚካሎች የተደራጁ እና ከማንኛውም አደጋ የተጠበቁ ቤተሙከራዎች ብዛት፣

መ) በኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍትና ጆርናሎች የተደራጀ ቤተመጽሐፍት እና

ሠ) የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦች (legislation)፣ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣይ ዓመት ስትራቴጂና ዕቅድ።

12.3) **የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላትን በተመለከተ**

1) ቀደም ብሎ የትምህርት ሚኒስቴርን ዝቅተኛ የብቃት መመዘኛዎችን አሟልቶ በኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

## 13. ስለ ደረጃ ስያሜ ጥያቄ አቀራረብ

13.1 የደረጃ ስያሜ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የደረጃ ስያሜ መጠየቂያ ማመልከቻና ይህ መመሪያ የሚጠይቃቸው ሰነዶች ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

13.2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 13.1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ/ የተቋሙ ስምና አድራሻ፣

ለ/ የሚፈለገው የደረጃ ስያሜ እና

ሐ/ ጥያቄውን ለማቅረብ ያነሳሳው አሳማኝ ምክንያት/justification/።

13.3 ኤጀንሲው የቀረበለትን የደረጃ ስያሜ ማመልከቻ መርምሮ በአዋጁና በዚሁ መመሪያ የሰፈሩትን መመዘኛዎች ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

## 14. የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ

14.1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የደረጃ ስያሜ አገልግሎት ክፍያ መንግስት ወደፊት በሚወስነው መሠረት የሚከናወን ይሆናል።